# የደም ድምጽ በህዳር ሌሊት ፲፱፷፯ ዓ/ም

*ይቺን ከዚህ በታች የከተብኳትን መጣጥፍ ያገኙሁት AFRICAN LIBRARY NOTES ከሚለው እአአ በሐምሌ 1977 ከታተመው ሲሆን የተረጎምኩትም ብዙ ያልተሰማ ነው ብዬ ብቻ ሳይሆን ይሄው በዚህ ወር ፴ ዓመታቸው ስለሚከበር የበኩሌን ለማስታወስ ነው። በተለይ ቀልቤን የሳበው እና እጅግ ያሳዘነኝ የቆጨኝ ብዙም የማይወራለትን የቀኃሥ ባለሥልጣኖች ሲረሸኑ ያሰሙትን የደም ድምጽ ሲሆን የተገኘው ከላይ በጠቀስኩት መጽሔት ቁጥር ፵ ላይ ነው። ፅሐፊው ያቀረቡት ዕውነተኛ ታማኝ ምንጭ ብለው ሲሆን የጠቀሱት ስም ወይም መለያ የለም። ስለዚህ እኔም እንደ ወረድ አቅርቤዋለሁ። እውነቱን የሚያውቁት ያዩና የተሳተፉት አሁንም በህይወት ይኖራሉ እንደ ማንኛውም የኢትዮጵያ ነገር ታሪክ ዕውነቱ ሳይወጣ ግፉና መከራው ስቃይና ዋይታው በላይ በላዩ እየተጨመረ ያለፈውን እንዳናንስታውስ ፋታ አሳርጥቶን ትውልዱ እንዳለ ያልፋል። ለምሳሌ የታህሳሱ ግርግር ተብሎ ስሙን አሳንሰው የሚተርኩት እንኳን በትክክል የሆነው ለታሪክ ቀርቦ አያውቅም ለዚህም ነው ሊቁ መንስግስቱ ለማ የፖለቲካ እስረኛ የነበሩ ግጥሞች ውስጥ ትሣሥ አቦ ላይ እንዲህ ያሉት፤-*

*ይቅርታ አድርግልን ወርቅነህ ገበዩ*
*አፍ አዊውን ዘልቀው ውስጣዊውን ያዩ።*
*ፊደል ከቆጠርነው ቀለሙን የለዩ።*
*ስንቱ ናቸውና?*

*ይቅርታም አትንፈግ ለነራስ አበበ፤*
*በወርቁ ሰልሰለት ታሥሮ በተሳበ።*
*ቦንብ እንደ እንቧይ ሲፈርጥ ባሩድ በዘነበ፣*
*ጊዜ መትረየሱን ጠምዶ የጠመደ፣*
*የፋሽስቱን ቀንበር ተኩላዋን ያረደ።*
*ጥይት እንኳን አከብሮት ከገላው ሲረግፍ፣*
*አስርት ጊዜ ተፋው ሞት እንኳን ከሱ አፍ።*
*ወርቅነህ ነህ አሉ ሰላይ ውስጥ አዋቂ*
*አስቲ አውጋኝ ታጣ እንዴ አቡን አስታራቂ።*
*ከቶ እንደምንድነው ታማኝስ መክዳቱ፣*
*ለጥቅሙስ ቀረ እንዴ አዳም መገዛቱ፡*
*በዕውነትስ ፡ሰማዕታት" ለሃይማኖት ሞቱ።*
*አሳየኝ ወዴት ነው የጭካኔ ቤቱ?*

*ይህን ታሪክ ያቀረቡት የተከበሩ አቶ ጌታቸው መካሻ ሲሆኑ በቀኃሥ መንግሥት በካይሮ የኢትይጵያ አምባሳደር ነበሩ። ደርግ የስልጣን ኮረቻ ላይ ሲፈናጠጥ ያገሪቱን አምባሳሰሮች በሙሉ ሲጠራ እሳቸውም ጥሪውን ተቀብለው ኢ. አ በገቡበት በዚያ በቀውጢ ሰዓት ነው ታሪኩን የሚተርኩት። እዚህ የቀረበው ቅንጭብ በጊዜው ስለነበረው ሁኔታ ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ እና ስለ ቀኃሥ መጻፍ የጀመሩት ገና ባልታተመ መጽኀፋቸው ነው። መጽሀፉንም ለተገኘ የተሻወርቅ ማስታወሻ እንደሆነ ተናግረዋል። እሱም ከጃዎቹ አንዱ ሲሆን የብስራተ ኢትዮጵያ የንግሊዝኛ ጋዜጣ አዘጋጅ የነበረ ነው) ወደ ታሪኩ እንግባ*

***የግድያው ሌሊት***

*በታላቁ የሚኒሊክ ቤተ መንግሥት ያቺ መጥፎ ቅዳሜ እንደ ማንኛውም ቀን ሌላ አሰልቺ እለት ነበረች። እስረኞቹ በቆይታቸው የለመዱት ነገር ስለሆነ የሚወጡና የሚገቡ ወታደሮችን ልብ ብሎ ማየት ትተዋል። መጻኢ ዕድላቸውና የእስሩ ሁኔታ በመሀከላቸው የነበረውን ልዩነትና ፉክክር ረገብ አርጎታል። በእስር ላይ በሚደርስባቸው በደል መጥፎ ነገር እንደሚደርስባቸው ይጠብቃሉ ተስፋ እንዲህ በቀላሉ አይጠፋም እና አንድ ታምር ነገር ተፈጥሮ እንደሚድኑ ያምናሉ። በትክክል ለፍርድ እንደሚቀርቡ ቃል ተገብቶላቸዋል ተስፍቸውን እዚህ ላይና የኢትዮጵያ ወታደር ሁልጊዜ ቃሉን ያከብራል በሚልና በውጭ እና በውስጥ የህዝብ ግፊት ላይ ተማምነዋል። ለዚህም ለመከላከያ የሚሆናቸውን ለማሰናዳት ሚስቶቻቸውን እና ጓደኞቻቸውን መረጃ እንዲሰበስቡላቸው ያስቸግራቸዋል።*

*ከምሽቱ ፪ ሰዓት ሲሆን ሁለት የተሸፈኑ (ቫን) መኪኖች እስረኞቹ ወዳሉበት ከመሬት በታች ያለ ቤት ደረሱ። ለረጂም ጊዜ እስረኞቹ ሁለት ክፍል የሆነ ብርሃን የሌለው እና እፍንፍን ያለ ቤት ውስጥ ነው የቆዩት። ጉዳያቸውን የሚከታተሉና ማንኛውን ኔገር በነሱ ስም የሚሰሩ እስረኞቹ ራሻቸው የመረጧቸው ሁለት ተወካዮች ወደ በሩ ተጠርተው ተጨማሪ ምርመራ ለማድረግ በሚል የጓደኞቻቸውን ስም ዝርዝር ይሰጧቸዋል። ሁለቱ ተወካዮችም ወሬቀቱን ይዘው ወደ ማደሪያቸ ሄደው ጮክ ብለው ስም ዝርዝሩን ያነባሉ። ስም ሲነበብ አንዳዶቹ ራት እየበሉ፣ ሌሎች ካርት ይጫወቱ ነበር። የተረፉት ለመኝታ እየተዘጋጁ ስለነብር ሁሉም ግን በሌሊት ልብሳቸው ነበሩ። ልብሳቸውን ለመለወጥ ጊዜ ሲጠይቁ አያስፈልግም ቶሎ ትመለሳላችሁ እያለ በትህትና የሚመልስላቸው የበላይ አዛዝ አለ። ስማቸው እየተጠራ ከስር ቤታቸው ሲወጡ የሚጠብቋቸው ወታደሮች አላስፈላጊ ሀይል እየተጠቀሙ እየመቱ በካቴና ጥንድ አርገው አሰሯቸው። ይህን ሁኔታ በብረት አጥር ጭላጭል ለማየት የሞከሩ ጥፊ ቀምሰዋል እና ጓደኞቻቸው ላይ አንድ መጥፎ ነገር እንደሚፈጸም ጠርጥረዋል።*

*የተሸፈኑት ሁለቱ መኪኖች በብረት ለበስና በታጠቁ ወታደሮች ታጅበው ፊታቸውን ወደ ኢቃቂ አለም በቃኝ አቀኑ። እስር ቤቱ በትላልቅ መብራቶች ቀን መስሏል። ጠባቂ ወታደሮች እየዘለሉ ወጥተው  እስረኞቹን እየጮሁ እንዲወርዱ አደረጓቸው። ከዚያም ሁሉንም መያዝ በማይችል አንድ ጠባብ ክፍል ሰበሰቧቸው። መትረየስ ያነገቡ የብረት ቆብ ያጠለቁት ወታደሮች ዙሪያቸውን ከበው እንደሚሞቱ የተነገራቸው እዚህ ቦታ ላይ ነው። አንድ የደርግ አባል ቶሎ ብሎ ወንበር ስቦ ወታደራዊው መንግሥት የህዝብ ጠላቶች በመሆናቸው የሞት ፍርድ እንደ ፈረደባቸው ፍርዱም ወዲያው እንደሚፈጸም ነገራቸው።*

***በድንጋጤ ተውጠው ከመሀላቸው ጠና ያሉት መስፍን ስለሺ***

*ተመልከት አንተ ወጣት ራሴን በሚመለከት ሙሉ ህይወት ኖራአለሁ ምንም የሚቆጨኝ ነገር የለም። እኔ ይህን ቀን እጠብቀው ነበር ሞትን በእቅፌ እቀበለዋለሁ። ዕድሜውን ሁሉ ላግሩ ያገለገለ ሰው የመጨረሻ መጥፎ ነገር የሚደርስበት በስተርጅና ውርደትን መቀበል ነው። እኔ አሁን ፷፰ ዓመቴ ነው አገሬ ይህ ረብሻ ከተነሳ ጀምሮ የማስበው በአንድ ጥይት ጭንቅላቴን ተመትቼ ለዘላለም ማረፍ ነው። በመጨረሻም ይህን ቃል ስለሰጣችሁኝ ምስጋናዬን ታላቅ ነው። ነገር ግን ከሚሞት ሽማግሌ አንድ ምክር ልስጣችሁ። የተማሩትን ወጣቶች እንዳልካቸውን እና እስክንድርን ማሯቸው። አንድ ቀን ላገሪቷ ይጠቅማሉ። በኋላ ይፀጽታችኋል። ቃሌን አትርሳ።*

**ጠ/ሚር አክሊሉ ሀ/ወልድ**

*እናንት ወታደሮች ለረጂም ዘመን ላገራችን የሰራነው በሙሉ በዕውነት ትክክል አይደለም ባይ ናችሁ። ይህን ማመን አልችልም ከሁሉም በላይ እናንተ ቢያንስ ለጋራ ጥሩ ነገር የሰራነውን እንኳን ትክዳላችሁ? እኔን የፈለጋችሁትን አድርጉኝ ላገሬ ግን ፈራሁላት።*

***እንዳልካቸው መኮንን***

*እኔ ላይ ምንም ጥፋት አታገኙም፡፤ የተማርኩ ከመሆኔ በስተቀር። አገሬን በሚቻለኝ ለማገልገል ሞክራአለሁ፡፤ ነገር ግን አይገባችሁም። ለምን መግደል አስፈለገ? የሚወዱትን አገር ማገልገል ዕውነት እንዲህ አይደለም።*

***አበበ ረታ***

*እናንተ ወታደሮች እጅግ ተሳስታችኋል። ኢትዮጵያን እጅግ ውስብስብ አገር ነች። ለችግሯ መፍትሄ ያረጋችሁት በጣም ቀላል ነው። ይቺን አገር እንደዚህ መግዛት አትችሉም። በከባዱ መንገድ ትማሩ ይሆናል።*

***አሰፋ ለያና***

*በዕውነት ማንን እንደምትገሉ ታውቃላችሁ ወይስ ተሳስታችሁ ነው? ስራዬ እንደ ወታደርም እንደ እኩል ደንብ (ሲቪል) የህዝብ አገልጋይም ግልጽ ነው። የንፁህ ሰው ደም ማፍሰሳችሁን ዕወቁት። ይህ ቅጥ ያጣ ዕብደት ነው።*

***ኮሞዶር እስክንድር ደስታ***

*ምን እደሚመጣ አውቄ ነበር እናም ይህን አገር ጥዬ ልጠፋ ነበር። ለኔ ሞት ንጉሠ ነገሥቱን አወግዛለሁ። ምክንያቱም ያለፍቃዴ በግድ እንድመለስ ስላረጉኝ።*

*ይህ የደም ድምጽ በዚያች ቀነ ጎደሎ ቅዳሜ ሌሊት ከመረሸናቸው በፊት የተናገሩት ነው የተኮሱትም ያስተኮሱትም እኔ ነኝ ባይሉም ለዕውነት የሚሞቱ ሰዎች አሁንም አይጠፉና ላገሪቷ ክብርና ታሪክ ሲሉ ቢተርኩት እጅግ ብዙ ጥቅም ይሆረዋል። መንግሥቱ ወይም ፍቅረ ሥላሴ ሌሎች ጓደኞቻቸው ይህን አይናገሩም እኔም አልጠብቅም። ከዚይ ውጭ ያሉ ሰዎች በቅርብ ለማየት ዕድሉ የነበራቸው አሁንም በህይወት ስላሉ ቁም ነገር ጥለው ቢያልፉ ባለ ውለታ ይሆኑ ነበር።*

*በቸር ይግጠመን*
*ክንፈ ሚካኤል*
*አውስትራሊያ*